# የአእምሮ ጤንነት፣ የንቃተ ህሊና ወይም የእድገት እክሎች ላሉባቸው ግለሰቦች የሚቀርብ ፍትሀዊ መኖሪያ ቤት




www.hud.gov/fairhousing

ይጎብኙ፣ ወይም በፌደራል የመረጃ መስመር ላይ ይደውሉ

1-800-669-9777 ወይም 1-800-877-8339 (የፌዴራል ሪሌይ)

Amharic

# የአእምሮ ጤንነት፣ የንቃተ ህሊና ወይም የእድገት እክሎች ላለባቸው ግለሰቦች የሚቀርብ ፍትሀዊ መኖሪያ ቤት



**ፍትሃዊ የቤቶች ህጎች** የአእምሮ ጤንነት፣ የንቃተ ህሊና  ወይም የእድገት እክል ያሉባቸውን ግለሰቦች ጨምሮ በአካል ጉዳተኞች ላይ የመኖሪያ ቤት አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። በአካል ጉዳተኝነት ላይ መሰረት ያደረገ የመኖሪያ ቤት መድልዎ ምሳሌዎች:

- በአካል ጉዳተኛነትዎ ምክንያት ለእርስዎ ለማከራየት ፈቃደኛ አለመሆን
- ተመጣጣኝ ማረፊያን ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆን ወይም ለእርስዎም ሆነ ወይም የአካል ጉዳት ላለበት አብሮዎት የሚኖር ሰው ቤትዎን በእኩል እድል ለመጠቀም ወይም በመኖሪያ ቤትዎ ለመደሰት አስፈላጊ ሊሆንብዎት የሚችሉ ምክንያታዊ ማሻሻያዎችን ያለመፍቀድ
- በአካል ጉዳተኝነትዎ ምክንያት ለእርስዎ ወይም ከእርስዎ ጋር አብሮ ለሚኖሩት ሰው ስለ መኖሪያ ቤት መረጃ ለመስጠት ወይም ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን
- በመኖሪያ ቤት ኪራይ ወቅት በአካል ጉዳተኝነትዎ ምክንያት ከፍ ያለ ኪራይ ወይም የዋስትን ተቀማጭ ገንዘብን የመሳሰሉ የተለያዩ ውሎችን ወይም ሁኔታዎችን ማስቀመጥ፣ ወይም ተጨማሪ መረጃን መጠየቅ
- በአካል ጉዳተኝነትዎ ምክንያት እርስዎን በተወሰኑ ክፍሎች ወይም በመኖሪያ ቤት ግቢ ውስጥ እንዳይኖሩ መገደብ
- በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት እርስዎን ወይም አብሮት የሚኖር ሰውን ማስወጣት
- በአካል ጉዳተኝነትዎ ምክንያት እርስዎን ወይም አብሮዎት የሚኖር ሰው ላይ ትንኮሳ ማድረግ

**ስለ ፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት መብቶችዎ የበለጠ ለመረዳት https://www.hud.gov/fairhousing ን ይጎብኙ።**

**የመኖሪያ ቤት መድልዎ አጋጥሞዎታል? ቅሬታዎን ለማስመዝገብ፥ https://www.hud.gov/fairhousing/fileacomplaint ን ይጎብኙ ወይም ለ HUD መስመርን በ 1-800-669-9777 (እንግሊዝኛ/ስፓኒሽ) ወይም 1-800-877-8339 (የፌዴራል ሪሌይ) ይደውሉ፡፡**

EQUAL HOUSING OPPORTUNITY

**ፍትሃዊ የቤት አቤቱታ ስላቀረቡ፣ የመኖሪያ ቤት አቅራቢው በእርሶዎ ላይ እርምጃ ከወሰደ ይህ ሕገ-ወጥ ነው።**



Amharic